

ነሐሴ/ 2013 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ይዘት

ክፍል አንድ:- አጠቃላይ ሁኔታ

1.1. ዓላማ

1.2. ወሰን

1.3. ትርጓሜ



ክፍል ሁለት:- የኤክሳይዝ ታክስ ምንነትና አስፈላጊነት እንዲሁም አከፋፈል

2.1. የኤክሳይዝ ታክስ ምንነት

2.2. የኤክሳይዝ ታክስ አስፈላጊነት

2.3. የታክሱ መጣኔ

ይዘት...

2.4. የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ጊዜ

2.5. ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የተደረጉ ዕቃዎች

2.6. የስሌት መሠረት

2.7. ወርሀዊ የዋጋ ዝርዝር አቀራረብ

2.8. የዕቃ ቆጠራ እና የጠፉ ዕቃዎች

2.9. የፋብሪካ መሸጫ ዋጋ

2.10. የጥሬ ዕቃ

2.11. የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች መጠን

ይዘት...

2.12. የፈሳሽ ዕቃዎች ብዛት ስለመለካት

2.13. በጥሬ ዕቃ/ግብዓት ላይ የተከፈለን ታክስ ስለማቀናነስ

2.14. የአልኮል ጥንካሬ መለካት

ክፍል ሶስት:- ስለፈቃድ

3.1. ፈቃድ ማግኘት የሚያስፈልጋቸው ሥራዎች

3.2. ለፈቃድ ማመልከቻ ስለማቅረብ

3.3. የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት

3.4. ፈቃድ ስለመስጠት

ይዘት...

3.5. የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ስለማግኘት

3.6. የፈቃዱ ቅርጽ

3.7. ፈቃድ የተሰጠው ሰው ግዴታዎች

3.8. አዲስ አምራቾች

3.9. ተጨማሪ ፋብሪካ ስለማቋቋም

3.10. ፈቃድን ስለማገድ

3.11. ፈቃድ የሚያሠርዙ ሁኔታዎች

ይዘት...

3.12. የፈቃድ መታገድ ወይም መሠረዝ የሚኖረው ውጤት

3.13. ፈቃድ ከመታገዱ ወይም ከመሠረዙ በፊት ስለሚሰጥ ማስጠንቀቂያ

3.14. ስለይግባኝ

ክፍል አራት:- የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር

4.1. የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ የሚደረግ ቁጥጥር

4.2. በቁጥጥር ሥር ያሉ ዕቃዎች በሚመለከት ፈቃድ የተሰጠው አምራች

ግዴታዎች

ይዘት...

4.3. የአልኮል ማጣሪያ ፋብሪካ ውጪ መሣሪያውን እንዲጠቀምበት ስለመፍቀድ

4.4. ከፋብሪካ ወጪ እንደተደረጉ የሚቆጠሩ ዕቃዎች

4.5. መሣሪያ/ቴክኖሎጂ ስለመግጠም

4.6. በጥሬ ዕቃ ላይ የሚደረግ ቁጥጥር

4.7. ዕቃዎች ከተመረቱ በኋላ በመጋዘን ስለማስቀመጥ ወይም ስለማስረከብ

4.8. የምርት መከታተያ ሥርዓት ክፍል

ይዘት...

አምስት:- የኤክሳይዝ ቴምብር

5.1. የኤክሳይዝ ቴምብር እና ሌሎች ምልክቶች

5.2. በማምረቻ ቦታዎች ወይም በማስተላለፊያ መስመሮች ላይ ምልክት ስለማድረግ

5.3. በምርቶች፣ በመያዣዎች እና በማሸጊያዎች ላይ ምልክት (ሌብል) ስለማድረግ

ክፍል ስድስት:- ስለተመላሽ

6.1. ተመላሽ

ክፍል ሰባት:- የኤክሳይዝ ታክስ አስተዳደር

ይዘት...

7.1. መዝገብ ስለመያዝ

7.2. የኤክሳይዝ ታክስን ስለማስታወቅ እና ስለመክፈል

ክፍል ስምንት:- የአስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣቶች

8.1. የአስተዳደራዊ ቅጣቶች

8.2. የወንጀል ቅጣቶች

ክፍል ዘጠኝ:- ታክስ ላለመክፈል የሚደረግ ስምምነት

ማጠቃለያ

ማጣቀሻ

1.1. ዓላማ

❑ ዋና ዓላማ

- በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ እና መመሪያ መሠረት ውይይት በማድረግ ኤክሳይዝ ታክስ ግብር ከፋዮች በሕግ በተቀመጠው አሠራር መሠረት ታክሱን ማሳወቅ እና መክፈል ያስችላል። ከዚህ ባሻገር፤ ታክሱን ለማጎበረሰቡ ግልጽ ማድረግ ነው።

❑ ዝርዝር ዓላማ

- የኤክሳይዝ ታክስ ምንነት እና አስፈላጊነት በመግለጽ ማስላት ይችላሉ፤

- በጥሬ ዕቃ ላይ የተከፈለ ታክስ የሚቀነስና የማይቀነስ እንዲሁም ተመላሽ የሚፈቀድባቸውን ግብይቶች ይለያሉ፤
- የኤክሳይዝን ታክስ ምዝገባ እና ፈቃድ እንዲሁም እገዳን እንዴት እንደሚከናወኑ ይገልፃሉ፤
- የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥርን እንዴት እንደሚከናወን ይገልፃሉ፤
- የኤክሳይዝ ታክስ እንዴት እና መቼ እንደሚከፈል እንዲሁም ታክሱን ላለመክፈል የሚደረግ ስምምነት ምን ማለት እንደሆነ ያስረዳሉ።
- የኤክሳይዝ ታክስ አስተዳደራዊ እና ወንጀል ቅጣቶች ይለያሉ።


1.2. ወሰን

- **የሰነዱ ሽፋን**

  - ሰነዱ የሚሸፍነው የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 እና መመሪያ ቁጥር 67/2013 ነው።

- **የሥልጠና ተሳታፊዎች**

  - ሥልጠናው መሠረታዊ እንደመሆኑ ለኤክሳይዝ ታክስ ግብር ከፋዮች እና በግብር ከፋዩ ዘርፎች ለማ ጠረ በዘርፎቱ ጠረ ተኛነተቹጡ የተ ገገጠለቹጡ በለሙየዎች ይሰጣል



- **ጊዜ**

1.3. ትርጓሜ



ስ.ቁ2

2.1. የኤክሳይዝ ታክስ ምንነት

ኤክሳይዝ ታክስ <u>የቅንጦት</u> ዕቃዎች፣ የህብረተሰቡን <u>ጤንነት የሚጎዱና ማህበራዊ ችግር የሚያስከትሉ</u> ዕቃዎችን አጠቃቀም ለመቀነስ ሲባል እንዲሁም ዋጋቸው ጨመረም አልጨመረም መሠረታዊ በመሆናቸው ምክንያት <u>የገበያ ፍላጎታቸው በማይቀንስ</u> ዕቃዎች ላይ ይጣላል። ኤክሳይዝ ታክስ የተጣለው:-

- በተፈቀደለት አምራች <u>በኢትዮጵያ ውስጥ የሚመረቱ</u> የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች እና <u>ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ</u> የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች።

ሰ፡3

2.2. የኤክሳይዝ ታክስ አስፈላጊነት




ሙከራ 1

- የኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ የስሌት መሠረት አብራራ/ሪ?

ቪ፡4

2.3. የታክሱ መጣኔ



በመኪናዎች ላይ ብቻ ግን የአገልግሎት ዘመናቸውን፣ የሲሲ መጠናቸውን መሠረት አድርጎ እስከ 500% ተጥሎባቸዋል። ሚኒስትሩ የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጣኔ ላይ ከ10% ያልበለጠ መጣኔ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል።

ሰ፡5



- በኢትዮጵያ ውስጥ የሚመረቱ፤
  - ዕቃዎች ከፋብሪካ በሚወጡበት ወይም ፋብሪካ ውስጥ ጥቅም ላይ በዋሉበት ጊዜ ሲሆን ታክሱ የሚቀጥለው ወር 30ኛው ቀን ከማለፉ በፊት ይከፈላል።
- ወደ ሀገር የሚገቡ ዕቃዎች፤ ወደ ሀገር በገቡበት ጊዜ፤
  - ከጉምሩክ ወደብ ሲወጡ ወይም ወደ ተፈቀደለት የጉምሩክ መጋዘን የሚገቡ ከመጋዘኑ ሲወጡ፣
- በኤክስፖርት ምርቶች ማምረቻ የሚመረቱ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ እንዲውሉ ሲወጡ፣

2.5. ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የተደረጉ ዕቃዎች

- የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያሟሉ ዕቃዎች:-

- አውሮፕላን በዓለምዐቀፍ ትራፊክ እንቅስቃሴ ውስጥ ባለበት ጊዜ በጉዞ ወቅት የሚጠቀሙባቸው በነፃ የሚሰጡ ዕቃዎች፤
- በዲፕሎማቶች መብትና ጥቅም ደንብ የተፈቀዱ ዕቃዎች፤
- የአካል ጉዳተኞች ወደሀገር እንዲያስገቡት የተፈቀደ ለአካል ጉዳተኞች እንዲያገለግል ሆኖ የተሠራ አንድ የግል ልዩ ተሽከርካሪ፤
- በአደጋ የተጐዱ ሰዎችን ለመርጃ እንዲውሉ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር ወደሀገር የሚያስገባቸው ዕቃዎች፤

ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ...

- ወደሀገር የሚገቡ መንገደኞች ይዘዋቸው የሚመጡ አግባብ ባለው ሕግ የተፈቀዱ ዕቃዎች፣ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ዕቃዎች፤
- ሚኒስትሩ በሚፈርመውወይም በሚያፀድቀው ስምምነት የተፈቀዱ በዕርዳታ ለሚካሄዱ ፕሮጀክቶች የሚያገለግሉ ወደሀገር የሚገቡ ወይም ከሀገር ውስጥ የሚገዙ ዕቃዎች፤
- የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር/የፌዴራልና የክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች ወደሀገር የሚያስገቧቸው ወይም ከሀገር ውስጥ የሚገዙዋቸው በሚኒስትሩ በሚወጣ መመሪያ የተፈቀዱ ዕቃዎች፤
- በአደጋ ወይም በሌላ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የጠፉ ወይም የተበላሹ ዕቃዎች፤

ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ...

- በኢንቬስትመንት ማበረታቻ ደንብ መሠረት ከቀረጥ ነፃ የሆኑ ኢንቬስተሮች ወደሀገር የሚያስገቧቸው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች፤
- በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ "ለ" የተዘረዘሩ ዕቃዎች (ከጉምሩክ ቀረጥ እና ከማናቸውም ታክስ ነፃ የሆኑ /ያልተመደቡ/)፤
- ከጥቅም ውጪ እንዲሆኑ የተደረጉ እና የገንዘብ ሚኒስቴር ነፃ የተደረጉ ዕቃዎች፤
- ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የመሆን መብት ላላቸው አካላት የሚሸጡ ዕቃዎች፤
- ለሕክምና አገልግሎት እንዲውል ለሰው በመጠጥነት አገልግሎት ሊሰጥ በማይችልበት አኳኋን የተመረተ አልኮል፤

ቪ፡7



- ወደሀገር ለሚገቡ ዕቃዎች፤
  - በጉምሩክ አዋጅ የሚሠላው የዕቃው ዋጋ እና
  - የጉምሩክ ቀረጥ ድምር
- በሀገር ውስጥ ለሚመረቱ ዕቃዎች
  - የፋብሪካ መሸጫ ዋጋ ሲሆን የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ የኤክይዝ ቴምብር (ካለ) ወጪ እና የተመላሽ ዕቃ መያዣ ወጪ አይጨምርም።

የስሌት ...

ምሳሌ:- አንድ የመኪና አስመጭ፤ የውጭ ምንዛሪው በኢትዮጵያ 400,000 ብር የሆነ የሲሊንደር ይዘቱ ከ1,000 ሲሲ ያልበለጠ አዲስ ሞዴል መኪና ከውጭ ሀገር ገዛ። ይህ አስመጭ ለትራንስፖርትና ሌሎች ወጪዎች 50,000 ብር አወጣ እና የመኪናው አጠቃላይ ወጪ 450,000 ብር ሆነ።

- የጉምሩክ ቀረጥ = 35%

የመኪና ጠቅላላ ዋጋ × የጉምሩክ ቀረጥ (450,000 × 35%) = 157,500 (የጉምሩክ ቀረጥ)

ኤክሳይዝ ታክስ = 5% (መኪናው አዲስ እና ከ1,000 ሲሲ ያልበለጠ ስለሆነ)

የስሌት...

ጠቅላላ ዋጋ + የጉምሩክ ቀረጥ (607,500) × ኤክሳይዝ ታክስ (5%) = 30,375

ኤክሳይዝ ታክስ = 30,375 (ከዚህ በኋላ ሌሎች ታክሶች/ቫት፣ ዊዝሆልዲግ፣ ... ይሰላሉ)

መከራ 2

- የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እና ነፃ የተደረጉ ዕቃዎች መጣኔ በመለየት ታክሱን በምሳሌ አስሉ?

2.7. ወርሀዊ የዋጋ ዝርዝር አቀራረብ

- የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት የሚከናወነው በዋጋው በመቶኛ ወይም በቁርጥ ወይም በሁለቱም ቢሆንም የተመረተው ምርት ብዛት በትክክል ሊመዘገብ እና ሪፖርት ሊደረግ ይገባል።
- የምርቱን ዋጋ ዝርዝር <u>በምርት ዓይነት፣ በመያዣው መጠን እና ዓይነት</u> እንዲሁም <u>ለገበያ በሚውልበት ቦታ</u> በመለየት ለታክሱ ባለሥልጣን በየወሩ ማቅረብ አለበት።
- ወርሀዊ የዋጋ ዝርዝር የሚዘጋጅበትና የሚቀርብበት ሁኔታ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለሚያመርቱ አምራቾች በተዘጋጀው ማንዋል ውስጥ በዝርዝር ይመለከታል።
- የእያንዳንዱን የምርት ዓይነት፣ የነጠላውን መጠን እና ዓይነት የሚያሳየው የዋጋ ዝርዝር የእያንዳንዱን ምርት <u>የማምረቻ ወጪ እና የትርፍ ህዳግ</u> የያዘ ሊሆን ይገባል።

ወርሀዊ የዋጋ...

- ዕቃው ለታክሱ ባለሥልጣን በቀረበው የዋጋ ዝርዝር ውስጥ ከተመለከተው ዋጋ በላይ የተሸጠ እንደሆነ ለኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሠረት የሚሆነው በደረሰኙ ላይ የተመለከተው ዕቃው የተሸጠበት ትክክለኛ ዋጋ ይሆናል።
- ዕቃው ለታክሱ ባለሥልጣን በቀረበው የዋጋ ዝርዝር ውስጥ ከተመለከተው ዋጋ በታች የተሸጠ እንደሆነ ወይም ከተፈቀደለት ፋብሪካ በሚወጣበት ጊዜ ዋጋው ያልተከፈለበት ከሆነ ከፋብሪካው በወጣው ዕቃ ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የሚሰላው በቀረበው የዋጋ ዝርዝር በተመለከተው ዋጋ መሠረት ይሆናል።

መርሀዊ የዋጋ...

- ዕቃው ከፋብሪካ በሚወጣበት ጊዜ የሚዘጋጀው የዕቃ ማስረከቢያ ሰነድ እና/ወይም ደረሰኝ የሚከተሉትን መረጃዎች ሊይዝ ይገባል:-

ሀ) ዕቃው ከፋብሪካው የወጣበት ቀን፣ የዕቃውን ማስረከቢያ ቦታ፣ የዕቃዎቹን ብዛትና ዓይነት፤

ለ) የደንበኛውን ስም ወይም ሽያጭ ከመከናወኑ በፊት ከፋብሪካ የሚወጣ ከሆነ እንዲሁም ደንበኛው ከተፈቀደለት አምራች ጋር ግንኙነት ያለው ሰው ከሆነ ይህንኑ፣

ሐ) የእያንዳንዱን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ዕቃ ዋጋ፣ ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ።

2.8. የዕቃ ቆጠራ እና የጠፉ ዕቃዎች

- አምራቹ በእያንዳንዱ የተፈቀደለት ፋብሪካ ውስጥ የሚገኙ ጥሬ ዕቃዎችን ጨምሮ በፋብሪካው ውስጥ በሚገኝ ዕቃዎች ላይ ወርሀዊ ቆጠራ ወይም በየዓመቱ የተሟላ ቆጠራ ማካሄድ አለበት።
- የተፈቀደለት አምራች ለውጭ ገበያ የተላኩ ዕቃዎችን የሚመለከት የተሟላ መረጃ መያዝ አለበት። ዕቃዎች የጠፉ መሆኑን የሚያረጋግጥ የዕቃው መጥፋት በታወቀበት ጊዜ ወዲያውኑ ሪፖርት የተደረገና አግባብ ባለው የፀጥታ አካል ምርመራ ተካሂዶ የዕቃው መጥፋት የተረጋገጠ ሲሆን ብቻ ነው።

የዕቃ ቆጠራ እና የጠፉ...



- መጥፋቱ ባልተረጋገጠ ዕቃ ላይ ተገቢው የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈላል። በእያንዳንዱ የተፈቀደለት ፋብሪካ ቆጠራ ከመካሄዱ ከ14 ቀን በፊት የታክሱ ባለሥልጣን ይህንኑ እንዲያውቀው መደረግ አለበት። ቆጠራ በሚካሄድበት ጊዜ በፋብሪካው ውስጥ የሚካሄድ ማናቸውም የሥራ እንቅስቃሴ መቆም አለበት።



- አምራቹ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች የሸጠው ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል በሚደረግ ግብይት ለገዥው የሆነ እንደሆነ፣ ገዥው የከፈለው ዋጋ፣
- በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ዕቃው ከአምራቹ ፋብሪካ በወጣበት ጊዜ ያለው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ነው።

2.10. ጥሬ ዕቃ

የተፈቀደለት አምራች <u>የመጨረሻውን</u> ምርት ለማምረት የሚጠቀምባቸውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ጥሬ ዕቃዎች ራሱ የሚያመርት እና የኤክሳይዝ ታክሱ ስሌት በዋጋው በመቶኛ በሚሆንበት ጊዜ የጥሬ ዕቃው ዋጋ ሆኖ የሚወሰደው <u>ትክክለኛው የገበያ ዋጋ</u> (ጥሬ ዕቃውን ለማምረት የሚወጣው <u>ወጪ</u> እና ዕቃው ለ3ኛ ወገን ቢሸጥ የሚታከለውን <u>የትርፍ ህዳግ</u>) ነው።

በሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃ ተጠቅመው የሚያመርቱ አነስተኛ የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፍሉ የተፈቀደ በሚሆንበት ጊዜ ጥሬ ዕቃው በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ እርሻ የተመረተ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ አለበት።

ቪ፡9

2.11. የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች መጠን

የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጠን የሚወሰነው ከዕቃው ጋር የሚሸጠውን የዕቃውን ማሸጊያ እና በውስጡ የያዘውን ክብደት መሠረት በማድረግ ይሆናል፤



2.12. የፈሳሽ ዕቃዎች ብዛት ስለመለካት

- የፈሳሽ ዕቃዎች ብዛት የሚለካባቸው 2 ደረጃዎች፤

I. በምርት ሂደት ውስጥ ፈሳሹ በጥቅል ተከማችቶ በሚገኝበት ጊዜ

II. ፈሳሹ በሚታሸግበት ጊዜ። ይህ ቢኖርም፤ ብዛትን የመቆጣጠሪያ ዘዴ "የአማካኝ ይዘት" ከሆነ በደረሰኙ ወይም በማስረከቢያው ሰነድ ላይ ከተመለከተው ያነሰ ሊሆን አይችልም።

- ፈሳሽ ምርቱን በማሸግ ሂደት የሚባክነው መጠን ተመዝግቦ መያዝ አለበት።
- ፈሳሽ የሚለካበትን ትክክለኛነት በየጊዜው ማስመርመር እና በሚጠይቅበት ጊዜ የምርመራው ውጤት መስጠት አለበት።

ቪ፡10

2.13. በጥሬ ዕቃ/ግብዓት ላይ የተከፈለን ታክስ ስለማቀናነስ

ጥሬ ዕቃዎች/ግብዓቶች የመጨረሻውን ምርት ለማምረት በግብዓትነት የተጠቀመባቸው ከሆነ፣ በጥሬ ዕቃዎቹ/ግብዓቶቹ ላይ የተከፈለው ታክስ በመጨረሻ ምርቶቹ ላይ ከሚከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ ጋር እንዲቀናነስ ይደረጋል። ይህ አልኮልን፣ ትንባሆን እና ስኳርን አይጨምርም።

ሙከራ ሶስት

- ❑ በጥሬ ዕቃ/ግብዓት ላይ የተከፈለ ታክስ የትኛው እንደሚቀነስና እንደማይቀነስ ለዩ?

2.14. የአልኮል ጥንካሬ መለካት

- የአልኮል መጠጦችን **በማብለላት** የሚያመርቱ ፋብሪካዎች የሚያመርቱት ምርት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት የአልኮል ጥንካሬውን መሠረት በማድረግ ከሆነ የእያንዳንዱን ምርት የአልኮል ጥንካሬ መለካት አለባቸው።
- **ከፍተኛ** የአልኮል መጠን መለካት ያለበት በአውቶማቲክ ዴንሲሜትር ነው። ከአውቶማቲክ ዴንሲሜትር ውጪ የሆነ ሌላ የመለኪያ መሣሪያ ጥቅም ላይ የዋለ ከሆነ፣ ይህ ዘዴ በኤክሳይዝ ፈቃድ ላይ መመልከት ያለበት።

3.1. ፈቃድ ማግኘት የሚያስፈልጋቸው ሥራዎች

- በኢትዮጵያ ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ማምረት፣
- የኤክሳይዝ ቴምብር ሊለጠፍባቸው ይገባል የተባሉ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ማቅረብ፣
- ሚኒስትሩ ፈቃድ የማግኘት ግዴታ በሚጥልባቸው ሌሎች ሥራ ዘርፎች መሠማራት።

3.2. ለፈቃድ ማመልከቻ ስለማቅረብ

- ማመልከቻው፤
  - በተፈቀደው ቅጽ መሠረት ሊቀርብ፣
  - የፈቃድ ክፍያ ሊከፈልበት፣
  - በባለሥልጣኑ በተወሰነው አኳኋን ሊቀርብ ይገባል።
- ማመልከቻ ሲቀርብ የታክሱ ባለሥልጣን የማምረቻ ቦታውን እና የአመራረቱን ሂደት ማመልከቻው ተሟልቶ በቀረበ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በቦታው በመገኘት መገምገም አለበት።

3.3. የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት

- ፈቃድ ሲጠየቅ መሟላት ያለበት:-
  - ማመልከቻው በተፈቀደው ቅጽ መሠረት መቅረብ አለበት፤
  - ከማመልከቻው ጋር ተያይዘው መቅረብ ያለባቸው መረጃዎች፤ ለምሳሌ:-
    - ✓ የንግድ ፈቃድና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣
    - ✓ የአመራረትና የአሠራር ሂደቶች እንዲሁም የማምረቻ ቦታዎች፣
    - ✓ የማምረቻ መሣሪያዎችን በማስረጃዎች፣ መግለጫዎች እና የማምረት አቅም።

3.4. ፈቃድ ስለመስጠት

- <u>መስፈርቶቹ</u> መሟላታቸው ሲረጋገጥ የኤክሳይዝ ታክስ <u>ፈቃድ ይሰጣል</u>።
- የታክሱ ባለሥልጣን አስፈላጊ መስሎ ከታየው የውል ቃሎችና ሁኔታዎች ወይም ገደቦች እንዲኖሩ ሊያደርግ ይችላል።
- የሚሰጠው ፈቃድ በታክስ ባለሥልጣኑ በተሰጠው ፈቃድ ላይ ከተመለከተው ቀን ጀምሮ የሚፀና ሲሆን ካልተሠረዘ በስተቀር ላልተወሰነ ጊዜ የፀና ይሆናል።

3.5. የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ስለማግኘት

- አምራቹ በፈቃዱ በተዘረዘሩ መሣሪያዎች ለመጠቀም የሚችለው በፋብሪካው በተመለከተው <u>አድራሻ ብቻ</u> ነው።
- አምራቹ ምርቶች የሚመረቱበትን አድራሻ ወይም መሣሪያ <u>ከመለወጡ</u> በፊት፣ ይህንኑ ለታክሱ ባለሥልጣን በ<u>ማስታወቅ</u> በፈቃዱ ላይ ማሻሻያ እንዲደረግ መጠየቅ አለበት።
- አምራቹ ፋብሪካ እና የማምረቻ መሣሪያዎች በአዋጁ የተደነገገውን የሚያሟሉ መሆኑ በታክሱ ባለሥልጣን ባለሙያዎች ጉብኝት ሳይረጋገጥ የኤክሳይዝ ፈቃድ ሊሰጥ አይችልም።

3.6. የፈቃዱ ቅርጽ

- ፈቃዱ የሚከተሉትን መያዝ አለበት:-
  - አምራቹ እንዲያመርት የተፈቀደለትን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን <u>ዕቃ ምድብ</u> ወይም ምድቦች፣
  - አምራቹ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች እንዲያመርት የተፈቀደለትን <u>ፋብሪካ</u>/ፋብሪካዎች::

3.7. ፈቃድ የተሰጠው ሰው ግዴታዎች

- የተሰጠውን <u>ፈቃድ</u> ዋንኛ ቅጂ የንግድ ሥራውን በሚያካሂድበት ዋና መሥሪያ በግልጽ በሚታይ ቦታ <u>መለጠፍ</u>፤
- ለታክስ ባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማስታወቂያ <u>መረጃዎችን</u> በጊዜው የመላክ፤

3.8. አዲስ አምራቾች

- የማምረት ሥራውን ለመጀመር ካቀደበት ቀን 30 ቀን በፊት የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ እንዲሰጠው ለታክሱ ባለሥልጣን ማመልከት።
- **የማመልከቻው ቅጽ** አዲስ የሚጀመረውን የንግድ ሥራ በሚመለከት የተሟላ መረጃ ማግኘት የሚያስችል መሆን በተለይም የንግድ ሥራው የሚመሩ ኃላፊዎች፣ የምርትና የግብዓቱን ዓይነት፣ ቦታ፣ የግብዓት ምርት ጥመርታውን እና የማምረቻ መሣሪያውን ዓይነት።

3.9. ተጨማሪ ፋብሪካ ስለማቋቋም

- በፈቃዱ ላይ ማሻሻያ እንዲደረግ ወይም አዲስ ፈቃድ እንዲሰጠው መጠየቅ፤
- የታክሱ ባለሥልጣን ባለሙያዎች የማምረቻ ቦታውን ጎብኝተው የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ከማግኘቱ በፊት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ማምረት መጀመር አይቻልም። ይህ ከሆነ፤
- ታክሱን መክፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ አስተዳደራዊና የወንጀል ቅጣት ይቀጣል።

3.10. ፈቃድን ስለማገድ

- የታክሱ ባለሥልጣን ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ የተሰጠውን ፈቃድ ማገድ ይችላል፡-

- ፈቃድ የተሰጠው ሰው ተገቢውን የሂሳብ መዝገብ ያልያዘ ወይም ማናቸውንም የተጣለበትን ግዴታ ያልተወጣ እንደሆነ፤
- ፈቃድ የተሰጠው ሰው በፈቃዱ የተመለከቱ ሁኔታዎችን የጣሰ እንደሆነ፤
- ፈቃድ የተሰጠው ሰው ለታክስ ባለሥልጣኑ የሀሰት ወይም አሳሳች መረጃን የሰጠ እንደሆነ፤
- አምራቹ በፈቃዱ ወይም በምዝገባው ከተመለከተው ውጪ በሆኑ ተግባራት ተሠማርቶ የተገኘ እንደሆነ

ፈቃድን የሚያሳግዱ ምክንያቶች...

- በፈቃዱ የተመለከተው ፋብሪካ፣ ማምረቻ ወይም መሣሪያ ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለማምረት ከዚያን ጊዜ በኋላ አጥጋቢ ሆነው ያልተገኙ እንደሆነ፤
- ከአምራቹ አቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም ሰው በተፈቀደለት አምራች የተመረተ የኤክሳይዝ ታክስ ያልተከፈለበት ዕቃ ይዞ የተገኘ እንደሆነ፤
- ፈቃድ የተሰጠበት ተግባር በአዋጁ/በሌላ ሕግ ከተከለከለ፣
- የተፈቀደለት የማምረቻ ቦታ ወይም መሣሪያ ከታክሱ ባለሥልጣን ፈቃድ ውጪ ተለውጦ የተገኘ እንደሆነ፣

3.11. ፈቃድ የሚያሠርዙ ሁኔታዎች

- የታክስ ባለሥልጣኑ ማስታወቂያ የደረሰው ከሆነ፣
- በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የፈቃዱን ዕገዳ በመቃወም ይግባኝ ያላቀረበ ከሆነ፣
- በተሰጠው ማስታወቂያ ወይም በታክሱ ባለሥልጣን በተሰጠ ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ ፈቃድ የተሰጠው ሰው በማስታወቂያው የተመለከተውን ሳያሟላ የቀረ እንደሆነ፣
- ፈቃዱ በመታገዱ ምክንያት የቀረበውን ይግባኝ የታክስ ባለሥልጣኑ ውድቅ ያደረገው ከሆነ።

3.12. የፈቃድ መታገድ ወይም መሠረዝ የሚኖረው ውጤት

- **አምራቹ፡-**
  - ዕቃዎች የማምረቱን ተግባር ወዲያውኑ ማቆም፣
  - በእጁ በሚገኙ እቃዎች ላይ ያልተከፈለውን ታክስ ወዲያውኑ መክፈል፣
  - ከታክሱ ባለሥልጣን በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በአምራቹ ፋብሪካ ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ማስወገድ አለበት።

ውጤት...

- **የታክሱ ባለሥልጣን:-**

- በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በታክሱ ባለሥልጣን ወደፀደቀ ቦታ እንዲያዘዋውር የማዘዝ።
- የአምራቹን ፋብሪካ እና በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች መያዝ ይችላል።
- በፈቃዱ መታገድ ወይም መሠረዝ ምክንያት ያወጣውን ወጪ እንዲተካ ፈቃድ ለተሰጠው ሰው የጽሑፍ ማስታወቂያ ሊሰጠው ይችላል።

3.13. ፈቃድ ከመታገዱ ወይም ከመሠረዙ በፊት ስለሚሰጥ ማስጠንቀቂያ

- ባለፈቃዱ ሊወሰድ የታቀደውን እርምጃ እንዲያውቀው ከ21 ቀናት በፊት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት አለበት።
- ፈቃድ የተሰጠው ሰው የወሰዳቸውን የማስተካከያ እርምጃዎች የሚመለከት ሪፖርት በደረሰው በ14 ቀናት ውስጥ የተወሰዱት እርምጃዎች በቂ መሆናቸውን ወይም በማስጠንቀቂያው የተገለፀ እርምጃዎች የሚወሰዱ መሆኑን ለመግለጽ ይችላል።

ሙከራ አራት

- የኤክሳይዝ ታክስ ምዝገባ እና ፈቃድ እንዲሁም እገዳን ግለጹ?

3.14. ስለይግባኝ

- የግብር ይግባኝ ኮሚሽን የቀረበለትን ይግባኝ መርምሮ ውሳኔ መስጠት አለበት።
- በግብር ይግባኝ ኮሚሽን የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት አለበት ብሎ የሚያምን ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የታክስ ባለሥልጣን ውሳኔው በተሰጠ በ30 ቀናት ጊዜ ውስጥ ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል።

ስላይድ 12

- የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር የሚደረገው ከሚከተሉት በቀደመው ጊዜ ይሆናል:-
  - ፈቃድ በተሰጠው አምራች ፋብሪካ ውስጥ የሚገኙ ዕቃዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ከፋብሪካው እስከሚወጡ፣
  - ዕቃዎቹ ከኢትዮጵያ ውጪ እስከሚላኩ፣ ወይም
  - ዕቃዎቹ ከአገልግሎት ውጪ እስከሚደረጉ ወይም እስከሚወገዱ ድረስ።

4.2. በቁጥጥር ሥር ያሉ ዕቃዎች በሚመለከት ፈቃድ የተሰጠው አምራች ግዴታዎች

- በፋብሪካው ውስጥ የመለኪያ ወይም የመቁጠሪያ መሣሪያዎች እንዲኖሩ እና በሚገባ እንዲጠበቁ ማድረግ፤
- በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የተሟላ ቁጥጥር ለማድረግ በሚያስችል መንገድ ማስቀመጥ፤
- የጥሬ ዕቃዎችን እና የመጨረሻ ምርቶችን ምዝገባ ማካሄድ፣ እና በየወሩ መጨረሻ የምዝገባውን ሚዛን ትክክለኛነት ማረጋገጥ፤
- የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው በፋብሪካው ውስጥ ጥቅም ላይ በዋሉ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለ መሆኑን ማረጋገጥ፤

4.3. የአልኮል ማጣሪያ ፋብሪካ ውጪ መሣሪያውን እንዲጠቀምበት ስለመፍቀድ

ከተፈቀደለት የአልኮል ማጣሪያ ፋብሪካ ውጪ የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያ እንዲይዝ ወይም እንዲጠቀምበት የሚፈቀድባቸው ምክንያቶች:-

- መሣሪያውን ለሽያጭ የሚያመርት ወይም የሚይዝ ሲሆን፤
- መሣሪያው የተያዘው ወይም ጥቅም ላይ የሚውለው ለሙከራ፣ ለጥናት ወይም ለሳይንሳዊ ምርምር ዓላማ ሲሆን፤
- መሣሪያው የተያዘው ወይም ጥቅም ላይ የሚውለው ከአልኮል መጠጦች ውጪ የሆነ ሌላ ምርት ለማምረት ሲሆን።

4.4. ከፋብሪካ ወጪ እንደተደረጉ የሚቆጠሩ ዕቃዎች

አምራቹ ባለሥልጣኑን በሚያረካ አኳኋን በፋብሪካው የተመረተውን ዕቃ ብዛት በማስረጃ ማረጋገጥ ያልቻለ እንደሆነ፣ በአንድ ወር ውስጥ ተመርቷል በተባለው እና ሊመረት ይችላል ተብሎ በሚታመነው መካከል ያለውን ዕቃ ከኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ውጪ ከፋብሪካው ወጪ እንዳደረገ ይቆጠራል።

4.5. መሣሪያ/ቴክኖሎጂ ስለመግጠም

- የተፈቀደለት አምራች በፋብሪካው ውስጥ የሚከናወነውን እንቅስቃሴ በሩቅ ማየት የሚያስችል የቴክኖሎጂ ሥርዓት መግጠም አለበት።
- የማምረት አቅም በሰዓት ከ500 ጠርሙስ በላይ ሲሆን በአውቶማቲክ የአመራረት ሂደት የታገዘ እንዲሆን ሊጠይቅ ይችላል።
- የመቁጠሪያ እና የመለኪያ መሣሪያዎች በምርቱ ሂደት በእያንዳንዱ የምርት ሠንሰለት ላይ መገጠም አለባቸው።

4.6. በጥሬ ዕቃ ላይ የሚደረግ ቁጥጥር

- ጥሬ ዕቃዎች ደህንነቱ በተጠበቀ ክፍል ወይም መጋዘን መቀመጥ አለባቸው።
- ለምርት ተግባር እንዲውሉ ለማድረግ ወይም አደጋ በማጋጠሙ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በታክሱ ባለሥልጣን ሳይፈቀድ ጥሬ ዕቃዎችን ማውጣት አይቻልም።
- የአልኮል ማጣሪያ ባለቤት ከኤቲል አልኮል በስተቀር ማናቸውንም ሌላ አልኮል ለሰው ጥቅም እንዳይውል ከመደረጉ በፊት በመጋዘን ማስቀመጥ አይችልም።

4.7. ዕቃዎች ከተመረቱ በኋላ በመጋዘን ስለማስቀመጥ ወይም ስለማስረከብ

- የማምረት ተግባር ከተጠናቀቀ በኋላ “የኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎች ማከማቻ” (የተጣራ አልኮል መቀበያ ጋኖች) በመባል ወደሚታወቅ ክፍል መዘዋወር እና ከተፈቀደለት ፋብሪካ ቅጥር ግቢ ውጪ እስከሚደረጉ ድረስ በዚሁ ክፍል ውስጥ መቀመጥ አለባቸው።
- ማከማቻ ክፍሉን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን የተመረቱ ዕቃዎች ከማከማቻነት ውጪ ለሌላ ለማናቸውም ተግባር እንዲውል ማድረግ አይቻልም።

በመጋዘን ስለማስቀመጥ ወይም ስለማስረከብ...

- አምራቹን ለይቶ ማወቅ የሚያስችለው ልዩ ምልክቱ (ሌብል)፣ የአምራቹ ስም፣ የተመረተበት ቦታ እና ቀን፣ አድራሻው፣ የተከታታይ ምርት ቁጥር፣ የባር ኮድ ወይም ሌላ ተጨማሪ ምልክት ሳይደረግበት ከማከማቻ ክፍል ማውጣት የለበትም።
- ለውጭ ገበያ ወይም ከታክሱ ነፃ ሆነው ሊሸጡ የተመረቱ ዕቃዎች ለቁጥጥር እና ለክትትል በሚያመች መንገድ ከሌሎች ዕቃዎች ተለይተው መቀመጥ አለባቸው።
- ከተሸጡ በኋላ ወደተመረቱበት ፋብሪካ የተመለሱ ዕቃዎች የሚቀመጡበት የተለየ መጋዘን ሊኖረው ይገባል።

4.8. የምርት መከታተያ ሥርዓት

- ባለሥልጣኑ፤ አምራቹ ወይም አስመጪው የምርት ሂደቱን መከታተል የሚያስችል የሂሳብ ሥርዓት እንዲዘረጋ ሊያዝ ይችላል።
- በማምረቻው ቦታ በምርት ሠንሰለት ውስጥ በእያንዳንዱ የማሸጊያ ወይም የማተሚያ መሣሪያ ላይ ሊገጠም እና ወደ ሀገር የሚገቡ ዕቃዎችን ለመቆጣጠር በታክሱ ባለሥልጣን በሚወሰነው አኳኋን ሊገጠም ይገባል።

ሙከራ አምስት

- የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥርን ገለጹ፤

5.1. የኤክሳይዝ ቴምብር እና ሌሎች ምልክቶች

የኤክሳይዝ ቴምብር ከመለጠፉ በፊት ማናቸውም ሰው፤

- የኤክሳይዝ ቴምብር ሊለጠፍባቸው የሚገባ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች፣
- ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ በሆኑ የአልኮል ምርቶች ላይ ቴምብር እንዲለጠፍባቸው ከተቀመጠበት ቦታ ማንቀሳቀስ አይችልም። ይህ ቢኖርም የታክሱ ባለሥልጣን በተለዩ ሁኔታዎችና ከሚኒስትሩ (ከገንዘብ ሚኒስቴር) አስቀድሞ ፈቃድ የተገኘ ሲሆን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የኤክሳይዝ ቴምብር ሳይለጠፍባቸው ከኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ውጪ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይችላል።

5.2. በማምረቻ ቦታዎች ወይም በማስተላለፊያ መስመሮች ላይ ምልክት ስለማድረግ

- “የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ማምረቻ” እና የተፈቀደለትን አምራች ስም እና የፈቃድ ቁጥር የያዘ ፅሑፍ መለጠፍ አለበት።
- በምርቱ ሂደት ጥቅም ላይ የሚውሉ የማስተላለፊያ መስመሮች በቋሚነት የተገጠሙ እና መላውን ርቀት በትክክል ለመመርመር የሚያስችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት።
- የማከማቻ እና የማስተላለፊያ መስመሮች ኢንዱስትሪው የሚጠየቀውን ደረጃ የሚያሟሉ መሆን አለባቸው።

ምልክት ስለማድረግ...

- የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች በሚመረቱባቸው፣ ለሽያጭ በሚዘጋጁባቸው ወይም በሚከማቹባቸው መሣሪያዎች ላይ በዘይት ቀለም ምልክት ማድረግ አለበት።
- የማስተላለፊያ መስመሮች በተለያየ የዘይት ቀለም (የአልኮል መጠጥ-ቀይ፣ ቢራ-ሰማያዊ፣ ሞላሰስ-አረንጓዴ፣ የሚጠራ ወይን-ቡናማ፣ ውሃ-ቢጫ፣ ናፍጣ-ጥቁር) እንዲቀቡ እና ቀለሙ እንዳይጠፋ ማድረግ እንዲሁም የመለኪያ ወይም የመቁጠሪያ መሣሪያ መግጠም።

ምልክት ስለማድረግ...

- የተፈቀደለት አምራች የታክሱን ባለሥልጣን በሚያረካ ሁኔታ እያንዳንዱን ማከማቻ ወይም መሣሪያ ለቁጥጥር እና ለክትትል በሚያመች አኳኋን ማስቀመጥ እና በውስጣቸው የያዙትን መጠን ማወቅ የሚያስችል የመለኪያ ወይም የመቁጠሪያ መሣሪያ የተገጠመባቸው እንዲሆን ማድረግ አለበት።
- መሣሪያዎችን ለመቆለፍ ወይም ለማሸግ በሚያስችል መንገድ ማዘጋጀት።
- ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር የአመራረቱን ሂደት ወይም አካሄዱን መለወጥ፣ ማከማቻ ወይም መሣሪያ መጨመር የለበትም።

5.3. በምርቶች፣ በመያዣዎች እና በማሸጊያዎች ላይ ምልክት (ሌብል) ስለማድረግ

- ከታክስ ነፃ የሆኑ፣ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ እና ሌሎች ዕቃዎች የተለየ ምልክት ሊደረግባቸው ይገባል። ለጅምላ ሽያጭ የሚውሉ ዕቃዎች በሚከተለው አኳኋን ህትመት ሊደረግበት ይገባል:-

  - ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ከሆነ፣ የመጨረሻ መድረሻውን ሀገር የሚያሳይ ጽሑፍ፣
  - በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ከሆነ፣ “ለሀገር ውስጥ ፍጆታ“ የሚውል የሚል ጽሑፍ፣
  - ከቀረጥ ነፃ የሆኑ ዕቃዎች ለሚሸጡበት መደብር ወይም ለዲፕሎማቲክ ሱቆች የሚሸጥ ከሆነ “ከታክስ ነፃ” የሚል ጽሑፍ::

ክፍል ስድስት:- ስለተመላሽ

6.1. ተመላሽ

- በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በፊት:-
  - ወደ ኢትዮጵያ በመጓጓዝ ላይ እያሉ ዕቃዎቹ ከጥቅም ውጪ የሆኑ ወይም የተሠረቁ፣
  - በቁጥጥር ስር ያሉ ዕቃዎች ከጥቅም ውጪ የሆኑ/የተሠረቁ፣
  - በሽያጭ ውሉ መሠረት ገዢው ዕቃውን ለሻጩ የመለሰ እንደሆነ፣ የተከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ ሊደረግ ይችላል።
- ታክሱ ከተከፈለ በኋላ ከታክሱ ነፃ የሆኑ ዕቃዎችን ለማምረት የዋሉ እንደሆነ፣ ታክሱ ተመላሽ ሊደረግ ይችላል።

ተመላሽ...

- የተመላሽ ጥያቄ፤ ዕቃዎቹ ከተሸጡበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር የ1 ዓመት ጊዜ ውስጥ፣/ ገዢው በሕግ የከሠረ መሆኑ በተረጋገጠበት ጊዜ ውስጥ ይቀርባል።
- ተመላሽ የተከፈለባቸው ዕቃዎች የተሸጡ/ከተፈቀደበት ዓላማ ውጪ ጥቅም ላይ የዋሉ እንደሆነ (ታክሱን በሙሉ/በከፊል የተቀበለ ከሆነ)፣ በተቀበለ በ30 ቀናት ውስጥ በተቀበለው መጠን ተመላሽ የተደረገለትን ለታክሱ ባለሥልጣን ይመልሳል።

ሙከራ ስድስት

- የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ ስለማድረግ የሕግ አግባቡን በማስረዳት ተመላሽ የሚፈቀድባቸውን ግብይቶች ለዩ?

ክፍል ሰባት፡- የኤክሳይዝ ታክስ አስተዳደር

7.1. መዝገብ ስለመያዝ

- የሂሳብ መዝገብ፣

➢ በሚነበብ እና ሊጠፋ በማይችል አኳኋን በጽሕፈት መሣሪያ የተዘጋጀ፣ የታተመ ወይም የተፃፈ ሊሆን የሚገባው ሲሆን፣ ከመፅደቁ በፊት የተደረገ እርማት ወይም ለውጥ ሲኖር የተደረገውን ለውጥ ወይም እርማት በትክክል ለማወቅ የሚያስችል፣ እርማቱን ያከናወነው ሰው ፊርማ እና የታረመበት ቀን የተፃፈበት፣

➢ በተፈቀደ አኳኋን በኤሌክትሮኒክ ወይም በሌላ መንገድ የተዘጋጀ እና በተፈቀደው አኳኋን ካልሆነ በስተቀር ለውጥ ያልተደረገበት መሆን አለበት።

7.2. የኤክሳይዝ ታክስን ስለማስታወቅ እና ስለመክፈል

- አምራቹ የእያንዳንዱን ወር ሂሳብ የሚቀጥለው ወር 30ኛው ቀን ከማለፉ በፊት ማስታወቅ አለበት።
- አስመጪ ወደ ሀገር ውስጥ ባስገባቸው የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ ሊከፍል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎቹ ወደ ሀገር በገቡበት ጊዜ ለታክሱ ባለሥልጣን መክፈል አለበት።

ሙከራ ሰባት

- የኤክሳይዝ ታክስ እንዴት እና መቼ ይከፈላል?

8.1. አስተዳደራዊ ቅጣቶች

- ፈቃድ ሳይኖረው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የሚያመርት፣
- የኤክሳይዝ ቴምብር ሊለጠፍባቸው የሚገባ ዕቃዎችን ቴምብር ሳይለጠፍባቸው የተገበያየ፣
- በፈቃዱ ከተመለከተው ቦታ ውጪ ሲያመርት የተገኘ፣
- ከኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ውጪ ዕቃ ወጪ አድርጎ የተገኘ፣ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ እጥፍ።

8.2. የወንጀል ቅጣቶች

- ፈቃድ ሳይኖረው የሚያመርት፣ የኤክሳይዝ ቴምብር ሳይለጥፍ የተገኘ፣ ከተፈቀደለት ቦታ ውጪ የሚያመርት-ከ3-5 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 50,000 እስከ ብር 100,000 በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል።
- በፈቃዱ ከተመለከተው ሥፍራ ውጪ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በማምረት ተግባር ላይ የተሠማራ-ከ5-7 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር 100,000-200,000 በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል።
- ፈቃድን እስከመታገድ የሚያደርስ ሁኔታ ከተገኘ-ከ1-3 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 100,000 ባልበለጠ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል።

የወንጀል...

- ታክሱ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ከቁጥጥር ውጪ ከማምረቻው ፋብሪካ ወጪ ያደረገ፣ ፈቃድ ሳይኖረው በታክሱ ቁጥጥር ሥር ያሉ ዕቃዎች ተከማችተው በሚገኙበት ቦታ የገባ፣ ባልተፈቀደ መንገድ ከተከማቹበት ቦታ ወጪ በማድረግ፣ ባህሪያቸውን በመለወጥ ወይም የቁጥጥሩን ሥራ በማወክ ረገድ የተባበረ-ከ5-7 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራትና ከብር 100ሺ-200ሺ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል።
- ስለኤክሳይዝ ቴምብር የተደነገገውን ተላልፎ የተገኘ- ከ2-3 ዓመት በሚደርስ እስራት እና ከብር 50ሺ-100ሺ በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል።

የወንጀል...

- ታክሱ ሳይከፈልባቸው ከተመረቱበት ፋብሪካ ወጪ የተደረጉ ዕቃዎችን የገዛ ወይም ሳይፈቀድለት እነዚህን ዕቃዎች የተቀበለ ወይም በይዞታው ሥር ያደረገ ወይም ታክሱ ያልተከፈለባቸውን ዕቃዎች ለሽያጭ በማዋል ተግባር የተሠማራ-ከ3-5 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 100,000-200,000 በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል።

ሙከራ ስምንት

- የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ እና በታክስ አስተዳደር አዋጅ የተጠቀሱትን አስተዳደራዊ እና ወንጀል ቅጣቶች ለዩ?

ክፍል ዘጠኝ:- ታክስ ላለመክፈል የሚደረግ ስምምነት

- የታክሱ ባለሥልጣን ታክስ ላለመክፈል ወይም ጥቅም እንዲያገኝ መሆኑን መረዳት የሚቻል ከሆነ፣ ስምምነቱ እንዳልተደረገ በመቁጠር የኤክሳይዝ ታክሱን እንዲከፍል ሊወስን ይችላል።
- ውሣኔው በ5 ዓመት ውስጥ መሆን አለበት።
- “የታክስ ጥቅም” ማለት:- ነፃ መሆንን ጨምሮ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ መቀነስ፣ ተመላሽ የማግኘት መብትን ማቋቋም፣ የሚከፈልበት ቀን ማዘግየት፣

መካከራ ዘጠኝ

- ታክሱን ላለመክፈል የሚደረግ ስምምነት ምን ማለት እንደሆነ አስረዱ?

ማጠቃለያ

- የኤክሳይዝ ታክስ መጣል አስፈላጊነት የኅብረተሰቡን ጤና ለመጠበቅ፣ በአካባቢ ደህንነት ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ዕቃዎችን አጠቃቀም መቀነስ፣ ገቢ ለመሰብሰብ እና ሀብትን ለማደላደል ነው።
- በዚህ ሥልጠና፤ የኤክሳይዝ ታክስ አከፋፈል፣ ስለፈቃድ፣ የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር፣ ስለተመላሽ፣ የኤክሳይዝ ታክስ አስተዳደር፣ የወንጀል ጥፋቶች እና አስተዳደራዊ ቅጣቶች እንዲሁም ታክስ ላለመክፈል የሚደረግ ስምምነት ተዳሰዋል።

ማጠቃለያ ...

❑ ኤክሳይዝ ታክስ ጋር ተያይዞ የተነሱ ዋና ዋና ጥያቄዎች እና መልሶቻቸው፤

- አንዳንድ ኢንዱስትሪዎች ምርታቸውን በቀጥታ በችርቻሮ ንግድ ሥራ ላይ ለተሠማሩ ድርጅቶች የሚያቀርቡ በመሆኑ የኤክሳይዝ ታክስ ስሌትና አከፋፈሉ ምን ሊሆን ይገባል?

ኢንዱስትሪዎች በችርቻሮ የሚሸጡትን ምርት ከፋብሪካው/ከመጋዘን በሚያወጡበት ጊዜ ኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታው የሚቋቋም ሲሆን፣ ከፋብሪካው በወጣው ምርት ላይ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የኤክሳይዝ ታክሱን የመክፈል ግዴታ አለባቸው።

ጥያቄዎች እና መልሶቻቸው...

- ከፋብሪካ ውጪ ምርታቸውን የሚሸጡ ኢንዱስትሪዎች፣ ዕቃዎች ለተጠቃሚው ጎብረተሰብ ለገበያ የሚያቀርብበትን ማናቸውም የሥራ ቦታ እንደፋብሪካ ይቆጠራል?

ፋብሪካ እንደሆነ የሚቆጠረው ምርቱ የሚመረትበት ወይም የሚከማችበት በፋብሪካው ቅጥር ግቢ ውስጥ ያለው ቦታ ነው። ከዚህ ውጪ ምርቶቹ ለተጠቃሚው የሚከፋፈሉበት ከፋብሪካው ቅጥር ግቢ ውጪ ያለ መጋዘን እንደፋብሪካ አይቆጠርም።

ማጣቀሻ

- የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 67/2013
- የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012


እመጣለሁ!
ኢሜይል፡-
morethiopia@gmail.com
ዩቲዩብ፡-
mor taxpayer education